በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# መንፈሳዊ አገልግሎት

## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ጳጉሜን ፬ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# መግቢያ

*በመንፈሳዊ አገልግሎት ዙሪያ የሚታዩ የተሳሳቱ አመለካከቶች*

1. አቅም ወይም ኃይል፡- በሌሎች ላይ ተጽእኖ ማሳደር እችላለሁ ወይም በሌሎች ላይ ሥልጣን አገኝበታለሁ ብሎ በማመን መጠቀሚያ ማድረግ፡፡

2. ክብርና ዝናን መፈለግ፡- በሄድኩበት ሥፍራ ወይም ለአገልግሎት በምገኝበት ቦታ ሁሉ ሰው ሁሉ ትኩረት እንዲሰጠኝ ምክንያት ይሆናል ኦ! አገሌ ይሉኛል ብሎ ማመን፡፡

3. ሞያ አድርጎ መቁጠር፡- ከ2፡30 — 11፡30 ድረስ እንደሚሠራ ሞያዊ ሥራ በመቁጠር በሰዓት ተገኝቼ የሚጠበቅብኝን ሥራ እሠራለሁ ከዚያ ባለፈ ምንም አይመለከኝም ወይም ለግል ሕይወቴ ምንም ድርሻ የለውም ብሎ ማመን፡፡

4. ማኅበራዊ ሕይወት፡- በአገልግሎቱ ብዙ ሰዎችን ባወቅሁ ቁጥር ከበርካታ ሰዎች ጋር መገናኘት ወይም መተዋወቅ የምችልበት ዕድል ይፈጠርልኛል ብሎ ማመን፡፡

5. ማስተማር፡- አንድ እውቀት ያለው ሰው ዕውቅት ለሌለው ሌላ ሰው ዕውቀቱን የሚያስተላልፍበት ዘዴ አድርጎ መቁጠር፡፡

*ታዲያ መንፈሳዊ አገልግሎት ምንድር ነው?*

- መንፈሳዊ አገልግሎት ጌታችን የሠራውን በምሳሌነትም ያስተማረንንም ማድረግ ነው፡፡
- "እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም፡፡" *ማር 10፡45፡፡*



# <u>የጌታችን ሥራ ምንድር ነው?</u>

1. ፍቅር።
2. መሥዋዕትነት ።
3. ድኅነት (ዘላለማዊ ሕይወት)።
4. ቅድመ ዓለም ከእግዚአብሔር ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን የተወለደ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ኢሳ 6)።
5. ለንስሐ መጥራት (የኃጢአት ሥርየት)።
6. መንፈሳዊ ምግብ

## <u>1. ፍቅር</u>

- "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" <u>*ዮሐ 3፡16።*</u>
- የእውነተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት መሠረት ነው።
- እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም የላከበት ምክንያት ነው።
- እንዴት መውደድ ወይም ማፍቀር እንዳለበት የሚያውቅ ሁሉ እንዴት ማገልገል እንዳለበት ያውቃል።
- አገልጋይ ድልድይ ነው።

# <u>የጌታችን ሥራ ምንድር ነው?</u>

## *2. መሥዋዕትነት*

- “በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።” *ኢሳ 53፡4-5።*

- አገልግሎት መሥዋዕትነት ነው።

- አግልግሎት ጊዜያችንን፤ የራሳችንን ድሎትና፤ ራሳችንንም መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ ነው።

- ቅዱስ ዮሐንስ፦ “እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።” እንዳለ - *ዮሐ 3፡30።*

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ “አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ። ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ።” እንዳለ - *2ኛ ቆሮ 11፡24-25።*

# የጌታችን ሥራ ምንድር ነው?

*3. ድኅነት (ዘላለማዊ ሕይወት)፡፡*

- "ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና፡፡" *ዮሐ 3፡17፡፡*

- አገልጋይ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ለራሱ እየኖረበት ለሌላው አሳልፎ የሚሰጥ ነው፡፡

- "ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው፥ ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ፡፡" እንዳለ - *ያዕ 5፡19-20፡፡*

*4. ቅድመ ዓለም ከእግዚአብሔር ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን የተወለደ የእግዚአብሔር መልእክተኛ መሆን*

- "እርሱም፦ ስለ ምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው፡፡" *ሉቃ 2፡29፡፡*

- "እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን፡፡" እንዳለ - *2ኛ ቆሮ 5፡20፡፡*

- "የጌታንም ድምፅ፡፡ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ፡፡ እኔም፡፡ እነሆኝ፥ እኔን ላከኝ አልሁ፡፡ እርሱም፦ ሂድ፥ ይህን ሕዝብ፡፡ መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉምም ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው አለ፡፡" *ኢሳ 6፡8-9፡፡*

# የጌታችን ሥራ ምንድር ነው?

*5. ለንስሐ መጥራት*

- “ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፦ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።” *ማቴ 4፡17።*
- አገልግሎት ንስሐን መስበክ ነው።
- አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው።
- አገልግሎት ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ቁልፍ ነው።
- አገልግሎት የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ነው።
- ንስሐ ወደ ተስፋና በሕይወትም ወደ መታደስ ይመራል።
- “ፈሪሳውያንና ጻፎችም። ይህስ ኃጢአተኞችን ይቀበላል ከእነርሱም ጋር ይበላል ብለው እርስ በርሳቸው አንጐራጐሩ። ይህንም ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ፥ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጐረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ። የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል። እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።” እንዳለ - *ሉቃ 15፡2-7።*

# የጌታችን ሥራ ምንድር ነው?

*6. መንፈሳዊ ምግብ*

- አገልግሎት ሌሎችን መንፈሳዊ ምግብ መመገብ ነው፡፡ ምግቡም ጌታችን ያስተማረን ትምህርት ነው፡፡
- በጥብርያዶስ ባሕር “ስምዖን ጴጥሮስ፦ ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው፡፡ እርሱም፦ እኛም ከአንተ ጋር እንመጣለን አሉት፡፡ ወጥተውም ወደ ታንኳይቱ ገቡ በዚያችም ሌሊት ምንም አላጠመዱም፡፡ በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆመ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም፡፡ ኢየሱስም፦ ልጆች ሆይ፥ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው፡፡ የለንም ብለው መለሱለት፡፡ እርሱም፦ መረቡን በታንኳይቱ በስተ ቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ አላቸው፡፡ ስለዚህ ጣሉት፤ በዚህም ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጐትቱትአቃታቸው፡፡ ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን፡፡ ጌታ እኮ ነው አለው፡፡ ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕር ራሱን ጣለ፡፡ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር ሁለት  መቶ ክንድ ያህል እንጂ እጅግ አልራቁም ነበርና ዓሣ የሞላውን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ፡፡ ወደ ምድርም በወጡ ጊዜ ፍምና ዓሣ በላዩ ተቀምጦ እንጀራም አዩ፡፡ ኢየሱስም፦ አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ አላቸው፡፡ ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባይቱ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶ የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህንም ያህል ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም፡፡ ኢየሱስም፦ ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው፡፡ ከደቀመዛሙርቱ አንድ ስንኳ፡፡ አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና፡፡ ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም ዓሣውን፡፡ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ሦስተኛው ጊዜ ነበረ፡፡ ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን፡፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ግልገሎቼን አሰማራ አለው፡፡ ደግሞ ሁለተኛ፡፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው፡፡ አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው፡፡ ሦስተኛ ጊዜ፡፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው፡፡ ሦስተኛ፡፡ ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፡፡ ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው፡፡ ኢየሱስም፦ በጎቼን አሰማራ፡፡” *ዮሐ 21፡3-17፡፡*

# የአገልግሎት ዓይነቶች

1. በቤ/ክን መዋቅሮች የሚሰጡና፤ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቶች
2. የታመሙ ሰዎችን ወይም ሽማግሌዎችን መጎብኘት
3. ድሆችን መጎብኘት
4. የታሠሩ ሰዎችን መጠየቅ
5. ቤተክርስቲያንን ማጽዳት ወይም መጠገን
6. መዝሙራትን መዘመር፤ መርሐ ግብሮችን መምራት
7. የቤተክርስቲያንን ትምህርቶች በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጎም
8. ወዘተ…

# በአገልግሎት የሚያስፈልግ ቁርጠኝነት

*ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ*

- “ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውስጥ ኖርሁ። ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።” *2ኛ ቆሮ 11፡25-27።*

*አባ እንጦንስ*

- ወደ ምንኩስና ሕይወት እንዲገባ ያደረገው ቁርጠኝነቱ ነበር። “ኢየሱስም፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።” የሚለውን ቃል ሲሰማ ቆርጦ ምንኩስናን መረጠ። *ማቴ 19፡21።*

*በዚህም የተነሳ የቆረጡት ሁሉ*

- ከእግዚአብሔር ጋር በሕይወታቸው ለማደግ በቅተዋል።
- ወደ ዓላማቸው ደርሰው ግባቸውን መትተዋል።
- ስለዚህ ቆራጥነት በአገልግሎት ዋናው ቁልፍ ነገር መሆኑን እንወቅ።

# ቁርጠኛ የሆኑ አገልጋዮች ምልክቶች

*1. የእግዚአብሔርን ሕግ ይጠብቃሉ ያከብራሉ፡፡*

- ዘወትር የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ ሌሎችም እንዲጠብቁ ያደርጋሉ፡፡
- ከእግዚአብሔር ሕግ ከወጡ ነገሮች ጋር ምንም ድርድር ሳያደርጉ በሕጉ ብቻ ይራመዳሉ፡፡
- ምሳሌ፡- አበ ብዙሃን አብርሃም ልጅህን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ ተብሎ ሲጠየቅ ያለ ምንም ማመንታት፤ ክርክርና ተቃውሞ ይስሐቅን አቀረበው፡፡
- "ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡" እንዳለ፡፡ *መዝ 118፡105፡፡*

*2. ውጫዊ በሆኑ ተጽእኖዎች ተጠልፈው አይወድቁም፡፡*

- ሎጥ በሰዶምና በገሞራ ሲኖር ራሱን በዚያ ከሚኖሩት ሰዎች ነውር ጠብቆ እንደ ነበር፡፡ *ዘፍጥ 19፡፡*
- ኖኅና ቤተሰቡ ክፋት በሠለጠነበት በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት እየኖሩ በደረቅ መሬት ላይ መርከብ እንደሠሩ፡፡ *ዘፍጥ 6፡፡*

*3. ራሱን በተለያዩ ነገሮች አያታልልም*

- ሦስቱ ወጣቶች በሞቱ እንደሚቀጡ ቢነገራቸውም ናቡከደነፆር ላሠራው ምስል አንሰግድም በማለት በዙሪያቸው ከሚገኘው ተጽእኖ ራሳቸውን በማትረፍ የቀረበላቸውን ፈተና አሸንፈዋል፡፡
- ነቢዩ ዳንኤል ምርኮና ቢሆንም ጾምን መርጦ የንጉሥን ምግብ አልበላም አለ፡፡ እኛስ በጾማችን ጊዜ ራሳችንን በማታለል ለጾም ማድረግ የሚገባንን አድልዎ እናጎድል ይሆን? *ትን. ዳንኤል በሙሉ ይነበብ፡፡*

# ቁርጠኛ የሆኑ አገልጋዮች ምልክቶች

*4. ለበደሉት በደል ከልብ ንስሐ ይገባሉ*

- ቁርጠኛ የሆኑ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ንስሐ የሕይወታቸው መታወቂያ ነው፡፡ ልብ አምላክ ዳዊት፤ ኢትዮጵያዊው ሙሴ፤ ግብጻዊቱ ማርያም ለዚህ ይጠቀሳሉ፡፡ *መዝ50፡1-ፍጻሜ፡፡*

*5. በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጋሉ*

- ሕይወታቸው ዘወትር እያደገ በመሄዱ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡
- ፈቃዳቸውንና ሕይወታቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ “ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፡፡” *1ኛ ቆሮ 9፡27፡፡*
- ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ ማንኛውንም መሥዋዕትነት ይከፍላሉ፡፡

*6. ጊዜያቸውን በአግባብ ይጠቀማሉ*

- አንድ ደቂቃ እንኳ ያለአግባብ ለሚጸጽታቸው ጉዳይ አያጠፉም፡፡ ለምን? ጊዜ ስጦታ ነውና፡፡
- አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አንድ በአማካይ የ70 ዓመት ዕድሜ ያለው ሰውከዕድሜው 20 ዓመቱን በእንቅልፍ፤ 20 ዓመቱን በሥራ፤ 6 ዓመቱን በመብላት፤ 7 ኣመቱን በመጫወት፤ 5 ዓመቱን ፊልሞች ወይም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በመመልከት፤ 5 ዓመቱን ልብስ በመልበስ፤ 3 ዓመቱን ኢተርኔት ወይም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፤ 1 ዓመት ስልክ በመጠቀም፤ 2.5 ዓመቱን ሌሎች ነገሮችን በማከናወን፤ 6 ወሩን ጫማውን በማሠር ይፈጃል ይላሉ፡፡ ታዲያ እግዚአብሔርን ማገልገሉ የት አለ?

# <u>ቁርጠኛ የሆኑ አገልጋዮች ምልክቶች</u>

*<u>ጊዜ</u>*

- ጊዜ የሕይወት ቅመም ነው፡፡ *<u>መክብብ 8፡፡</u>*
- አንድ ሰው ጊዜያችንን ከርሱ ጋር እንድናሳልፍ ሲጠይቀን የሕይወታችን ድርሻ ለመጋራት እንደጠየቀን እንረዳ፡፡
- ጊዜያችንን ያለአግባብ የምናጠፋ ከሆንን የምናጠፋው ሕይወታችንን እንደሆነ እንወቅ፡፡
- ጊዜያቸውን በአግባብ የሚጠቀሙበት ጊዜያቸውን ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት፤ የመጻሕፍትን ትርጉም በማጥናት፤ መጽሐፍ ቅዱስን ሌሎችንም መንፈሳውያን መጻሕፍት በማንበብ፤ አምልኮተ እግዚአብሔርን በመፈጸምም ጭምር ይጠቀሙበታል፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት "እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ፡፡" እንዳለ ይህንም በፍርሃትና በትሕትና ይፈጽሙታል፡፡ *<u>መዝ 5፡7፡፡</u>*

*<u>7. መዋዠቅ የሌለበት ቀጥተኛ ጉዞ አላቸው</u>*

- ቀጥተኛነት አንድን ነገር መለዋወጥ ሳይኖር ማከናወን ሲሆን ይኸም በየትኛውም የሕይወታችን አቅጣጫ የሚያስፈልገን ነው፡፡ በት/ቤት፤ በሥራ ገበታ፤ በስፖርት፤ ወዘተ እንደሚያስፈልጉ ሁሉ በመንፈሳዊ አገልግሎትም አንዴ ከፍ በሌላ ጊዜ ዝቅ እያሉ እየዋዠቁ መጓዝ አይጠበቅም፡፡

- በመጨረሻም ነቢዩ ኤርምያስ *<u>ኤር 4፡19፡፡</u>* *"አንጀቴ! አንጀቴ! ልቤ በጣም ታምሞአል፥ በውስጤም ልቤ ታውኮብኛል ነፍሴ ሆይ፥ የመለከትን ድምፅና የሰልፍን ውካታ ሰምተሻልና ዝም እል ዘንድ አልችልም፡፡"* እንዳለ ይኽን ቃል ሰምተን ዘወትር ያለ መንፈሳዊ ሥራ በተገኘን ጊዜ ሁሉ ባለቤቱ ይቀስቅሰን፡፡ *<u>አሜን!!!</u>*

የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ወርቃማ ቃል፡-

## *“ለኀሊናውና ለእውነት የሚኖር እርሱ የእግዚአብሔር አምሳል ነው”*

ይህ ቃል የአዲሱ ዓመት የዘመነ ማርቆስ (2002 ዓ.ም.) ወርቃማ ቃል ሆኖ ቃሉን እየተማርን ፈጽመንም በእውነት እያገለገልነው እንድንኖር አምላካችን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

መልካም አዲስ ዓመት ይሁንልን።